# ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም!

ከሃብሮማይ 08/07/09
ghabrom@yahoo.com

ሰዎች በተፈጥሯቸው የተለያየ የአየር ንብረት ያለውን አከባቢ የሚለምዱት ቀስ በቀስ መሆኑ ይታወቃል፡፡በደጋማ አከባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወደ ቆላማ አከባቢ ሲመጡ፤ለመኖር ያስቸግራቸዋል፡፡ቀስ በቀስ ግን አየሩ እየለመዱት ይሄዳሉ፡፡በተመሰሳይም በቆላማ አከባቢ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችም ወደ ደጋማ ስፍራ ሲሄዱም እንደዛው! ይህን የሚገለፀው ግን በሰዎች ብቻ ሳይሆን በማንኛውም ህይወት ያላቸው ነገሮች ጭምርም ነው፡፡ህይወት የሌላቸውንም አከባቢያቸውን በሂደት የሚለማመዱ አሉ፡፡ ለምሳሌ በአንድ ብርጭቆ ውስጥ ቀዝቃዛ ውሃ ቢኖርና ቀዝቃዛውን ደፍተህ በአፋጣኝ ትኩስ ውሃ ብትጨምርበት ብርጭቆውን ይሰበራል፡፡ ትኩሱ ውሃ ወደ ብርጭቆው ቀስ በቀስ ከጨመርከው ግን አይሰበርም፡፡ምክንያቱም ብርጭቆውም አከባቢውን ቀስ በቀስ ስለሚለምደው!

የስነ ልቦና ምሁራን ስለ ሰው ፀባይና ባህሪይ ሲገልፁ “ያደግክበትን አከባቢ ድምር ውጤት ነው” ይላሉ፡፡ ከአከባቢያችን ቀስ በቀስ የምንለምዳቸው ነገሮች ከልጅነታችን ጀምሮ የምናገኛቸው ባህላዊ፤ ሃይማኖታዊ፤ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ያንፀባርቃሉ፡፡

እኔ አሁን ትኩረት አድርጌ ለመፃፍ ያሰብኩት የሚኖርበትን አከባቢ በሰው ፖለቲካዊ አመለካከት ላይ የሚፈጥረው ተፅዕኖ ላይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው አገራችን ለብዙ ዘመናት በተለያዩ ስርዓቶች ስትተዳደር ቆይታለች፡፡ ፅሁፌ ተደራሽ እንዲሆን የንጉሱና የደርግ ስርዓትን መርጫለሁ፡፡ምክንያቱም ቢያንስ 50 ዓመትና ከዛ በላይ ያሉት ሰዎች የሁለቱ ስርዓቶች በአገሪቱ ላይ የነበራቸውን አገዛዝ ስለሚያውቁት!

አገራችን በነዚህ ስርዓቶች ዜጎቿ ክፉኛ ሲሰቃዩና ደማቸው በየጎዳናው እየፈሰሰ በፀረ ዴሞክራሲ አገዛዝ ስትማቅቅ መቆየቷ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው፡፡እነዚህ ህዝቦች የስርዓቶቹ ክፉኛ አገዛዝ በላይ በላያቸው ሲጫን፤ የጭቆና ቀንበሩ ከአንገታቸው አሽቀንጥረው ለመጣል ሌላ ሁለተኛ አማራጭ ወዳልነበረው የትጥቅ ትግል ገብተው ፀረ ዴሞክራሲያውንን ጠራርገው የዴሞክራሲ ፋና እውን አድርጓል፡፡

በሽግግሩ ጊዜ በአገራችን ዴሞክራሲ ለማስፈን ቆርጦ የተነሳውና አካሉና ህይወቱ ከፍሎ ይህን ዕድል የከፈተ ፓርቲ ብቻውን ያለ ማንም ተቃናቃኝ የስልጣን ወንበር ለመቆናጠጥ አልፈለገም፡፡ምክንያቱም ከመጀመርያ ሲነሳም በዴሞክራሲያዊ አኳሃን ህዝባዊ የሆነ መንግስት ለመመስረት እንጂ ስልጣንን ለመቆናጠጥ ስላልነበረ!

ስለሆነም የፀረ ዴሞክራሲ የበላይነት በኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ሰሪነት ሲገረሰስ የዴሞክራሲ ስርዓት የበላይነቱን መያዝ የግድ ነበርና ፤ ይህንን ለማረጋገጥ የተለያየ ዓላማ ያላቸው ፓርቲዎች እንዲሳተፉ ሆነዋል፡፡እዚህ ላይ አሁን በስልጣን ያለውን ፓርቲ ለአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ቁርጠኝነቱ በማያሻማ መንገድ ያረጋገጠበት አጋጣሚ ነበር፡፡ለምሳሌ ያህል ኢህአፓና ኢድዩ በተለያዩ ጊዜያት ኢህአዴግን ለማጥፋት ጦርነት አውጀዋል፡፡ብዙ ጊዜም ጦርነት ከፍቷል፡፡ ሁለቱም ፓርቲዎች ህዝባዊ መሰረት ስላልነበራቸው መሸነፋቸውን ግድ ሆነ፡፡ይሁን እንጂ ኢህአዴግ በአገሪቷ የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት ወደ ኋላ የማይል ፓርቲ ስለሆነና መለያ ባህሪውም እሱ ስለነበር የሽግግሩ መንግስት ሲመሰረት የተለያየ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች ጥሪ ቀርቦላቸዋል፡፡ከነዚህም መካከል መኢሶን፤ ኢህአፓ፤ኢድዩ፤ኦነግ እንዲሁም በወንጀል ያልተሰማሩ የደርግ ባለስልጣናት ጭምር ናቸው፡፡ይህ የሚያሳየው የአሁኑ ገዢው ፓርቲ ከመጀመርያም እንዴት ዴሞክራሲያዊ እንደነበር ነው፡፡

አሁን በአገራችን የሕገመንግስቱ የበላይነት የተረጋገጠበት፤ የአገሪቷ የስልጣን ባለቤት የኢትዮጵያ ህዝቦች ፤ብሄሮችና ብሄረሰቦች መሆናቸው የታመነበት

ህዝቦች የሚወክሏቸው በቀጥታ የሚመርጡበትና ወኪሎቻቸውም በአገሪቷ የበላይ ስልጣን ያለውን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሆነው የአገሪቷ ህግ የሚያፀድቁበት አገር ላይ እንገኛለን፡፡

ይሁን እንጂ በአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ላይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የዴሞክራሲ ሂደቱ አጋር እየሆኑ አይደሉም፡፡

የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአብዛኛዎቹ በበላይነት የሚመሩት ያሉ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት በደርግም ሆነ በሃይለስላሴም በተለያዩ ከፍተኛ የስልጣን እርከኖች የነበሩና አሁን ያለውን ስርዓት በተለያየ መንገድ እየታገሉ የነበሩ ሃይሎች መሆናቸው ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው፡፡

እነዚህ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ለብዙ ዓመታት በአፋኝና ፀረ ዴሞክራሲ ስርዓቶች ያለፉ ከመሆናቸው ባሻገር በነበረው ስርዓት ውስጥ በተለያዩ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ሆነው ስርዓቱን በመምራት ላይ የነበሩ በመሆናቸው ደግሞ የፀረ ዴሞክራሲ ባህሪያቸው በምን ደረጃ ላይ መሆኑ መገመት የሚከብድ አይመስለኝም፡፡

እርግጥ ነው ማንም ሰው አንድ አስተሳሰብ ከያዘ ይዞት የነበረውን አስተሳሰብ አሽቀንጥሮ ጥሎ ሌላ አስተሳሰብ ለመያዝ ይከብደዋል እያልኩ እንዳልሆንኩ አንባቢው ሊገነዘብልኝ እፈልጋለሁ፡፡ይሁን እንጂ ፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ትክክለኛ አስተሳሰብ ነው ብሎ ከመጀመርያ ያመነበትና ይህን አካሄድ ስህተት ነው ተብሎ ቢነገርበትም <ከደሙ ጋር ተዋህዶ አልለቅ> የሚለው እንዳለ ግን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ይህን የሚሆነው ፀረ ዴሞክራሲ አካሄድ ትክክለኛ ነው ብሎ ላመነ ሰው እንጂ መቀየር ለሚፈልግ ዓይነት ሰው እንዳልሆነ ግን ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡

ይህን ለማለት ያስገደደኝ የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው ላይ ያላቸውን ሚና ሳስብ፤ እስካሁን ድረስ ያላቸውን

እንቅስቃሴ ስገመግም ለአገሪቷ ይጠቅማታል ብለው ያወጡት ፖሊሲና ስትራተጂ በግልፅ አለማሳወቃቸው፣አባላቸው እንዴት መመልመል እንዳለባቸውና የአባሎቻቸውን የስነምግባር መመርያ በግልፅ ያለማስቀመጣቸው የውስጥ ችግር እንዳለባቸው በግልፅ የሚያሳይ ነው፡፡ አባል ሲመለምሉም ፖሊሲያቸውና ስትራተጂያቸውን አሳውቀውና አሳምነው ሳይሆን አደገኛ የፕሮፓጋንዳና የኮምዩኒኬሽን ስልት በመጠቀም በስሜትና ባልሆነ መረጃ በማሰባሰብ በመሆኑ ፓርቲዎቹ ተቋማዊ ይዘት እንዳይኖራቸው አድርገዋል፡፡

ይህ ስለሆነ ነው ተቃዋሚዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠነከሩና እየጎለበቱ መምጣት ሲገባቸው፣ ለአገራችን የዴሞክራሲ ሒደት የራሳቸውን አስተዋፅኦ ከማድረግ ይልቅ አንዴ ውሃ አንዴ እሳት እየሆኑ፣ነፋስ በነፈሰው ሁሉ እየተጓዙ አንደኛው የሆነ አቋም ሲይዝ ሌላኛው ማኩረፍ፣ስብሰባ ረግጦ መውጣት፣ በውስጣቸው የመቻቻል መንፈስ ዜሮ መሆን፣ስለአገሪቷ ከማሰብ ይልቅ ግለሰብ ከግለሰብ መናቆር ባህሪያቸው ሆኖ እየታየ ያለው፡፡

በዚህ የተነሳም አገራችን እንዴት ከድህነት እናላቅቃት ምን ዓይነት ፖሊሲና ስትራተጂ ከተከተልን ነው አገራችን ካለችበት እድገት በላይ ልናሳድጋት የምንችለው ብለው ተጨባጭ ፖሊሲና ስትራተጂ መቅረፅና ፍልስፍናቸውን ማሳየት ተስኑዋቸዋል፡፡አንዳንዴ ግራ ሲገባቸው መንግስት በሚሰራቸው ያለ ስራዎች ተሞርክዘው በሚያጋጥሙት የአፈፃፀም ችግሮች በመተቸትና የባለስልጣናትን ንግግር በማዳመጥ ከንግግሮች አንድ ቃል አውጥተው በማራገብ የተጠበዱበት አጋጣሚም ትንሽ አይደለም፡፡መተቸቱ ጥሩ አይደለም እያልኩ አይደለሁም፡፡ትልቁ ስራቸው ግን ይህ መሆን የለበትም ፡፡ይልቁንም አማራጭ የሚሉትን ፖሊሲና ሰትራተጂ ለህዝብ ማቅረብ አለባቸው ማለቴ ነው፡፡

ይህ የሆነው ለምንድነው? በአገራችን ለምንድነው እስካሁን ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ ያልተፈጠረው? የሚሉትን ጥያቄዎች በተገቢ መመለስ ያለባቸው ጉዳይ ይመስለኛል፡፡

ዋነኛውና ቁልፍ የችግሩ ምንጮች ከድሮ ጀምሮ በፀረ ዴሞክራሲ አካሄድ ለብዙ ዓመታት ተጣብቀው የኖሩና ፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ ሆነው እየመሩ የነበሩ ግለሰዎች ናቸው ካልኩ የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡አብዛኛው የተቃዋሚ ፓርቲዎቻችን የሚመሩት ከሃይለስላሴ ጀምሮ እስከ ደርግ በከፍተኛ የስልጣን እርከን የነበሩ ናቸው፡፡

እነዚህ አመራሮች በፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ለብዙ ዓመታት አምነውበት ሲሰሩ የነበሩና ከደማቸው ጋር ተዋሃህዶ ባህሪያቸው ሁሉ በፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የታጠረ ይመስለኛል፡፡አገሪቱ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ጀማሪ በመሆኗ ኅልብቶ ባሕል እስኪሆን ችግሮች ሊኖሩ ቢችሉም፣ እነዚህ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሆን ከሚገባው ያፈነገጡ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አካሄዶች እየታየባቸው ናቸው፡፡

እነዚህ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ከቀደምት የመንግስት ስርዓቶች ጋር አብዛኛው ዕድሚያቸው ስላሳለፉ ከነበሩት ስርዓቶች ባላቸው የስሜት ቁርኝነት ከፀረ ዴሞክራሲ አመለካከታቸው ጋር ሙጥኝ ያሉ ፤ አሊያም የስርዓቶቹ መጥፋት ቁሳዊ ፋይዳ አሳጥቷቸው ምክንያታዊ ያልሆነ የመጠቃት ስሜት ያደረባቸው ናቸው ካልኩ ሐቁን እየደበቅኩ አይደለሁም፡፡

እነዚህ ፓርቲዎች በልዩነት ውስጥ ያለ የዴሞክራሲ አጋርነትን ስተው በጥላቻ ስሜት ላይ ተዘፍቀው አገሪቷ የምታስመዘግበው ያለ የኢኮኖሚ ዕድገትና የዴሞክራሲ ግንባታ ጥላ ሸት በመቀባት፤የአገሪቷ ገፅታ በማበላሸት ላይ መጠመዳቸው ቀጥለዋል፡፡ በሌላም ሕገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ ሕዝብን አነሣስቶ በኃይል የመንግስት ሥልጣን ለመያዝ ተደርጐ የነበረው ሙከራ የከፋ ኢ - ዴሞክራሲያዊ አካሄድ እንደነበር በጉልህ የሚያሳይ ተጨባጭ ማስረጃ ነው፡፡

አረ! የአገራችን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባህሪያቸው ሆሉ ለአናርኪዝም የተመቸ ሆነዋል፡፡የቀድሞ የፈረንሳይ ታዋቂ ፖለቲከኛና አናርኪዝምን ከጸነሰሱ ዋነኛዎቹ ተብለው ከሚነገርላቸው አንዱ ጆሴፍ ፕሮድሃን ስለ አናርኪዝም ሲገልፅ

አናርኪዝም ማለት አንድ አገር መንግስት አያስፈልጋትም፤አገሪቷ ያለ ሕግና ያለ ስርዓት መንቀሳቀስ አለባት፤ማንኛውም ሰው ለራሱ በመሰለው ሁሉ የሌላውን መብት ግምት ውስጥ ሳያስገባ እንደፈለገ መሆን አለበት ይላል፡፡ የኛ አገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች ደግሞ ሕገ መንግስቱን ለመናድና መንግስትን በሃይል ለመጣል በተካሄደው ሴራ ተሳትፈው ህይወታቸውን ያለፉ ሰዎች ሕገ ወጥነታቸውን በማወደስ "ሰማዕታት" በማለት መኢአድና አንድነት ፓርቲዎች መዘከራቸው፤ ሕገ መንግስቱ ለመናድ ከሞከሩና እድሜ ልክ እስራት ከተፈረደባቸው ከዚያም በቅድመ ሁኔታ የተመሰረተ ይቅርታ ከተደረገላቸው መካከል አንዷ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ይቅርታ አልጠየቅኩም በማለታቸው በሕጉ መሰረት የተሰጣቸውን ይቅርታ እንዲነሳ ተደርጎ ወደ ማረምያ ቤት በመግባታቸው ፤ የአገራችን ተቃዋሚዎች ወንጀለኛዋ በማወደስና በማሞገስ በየወሩ ማክበራቸው፤በቅርቡ የወጣው የአገራችን የጸረ ሽብርተኝነት አዋጅ በሰፊው መኮነናቸው ከዚያም አልፈው ሕጉ ራሱ "ሽብር" ነው ማለታቸው፤ቀቢጸ ተስፋ የሽብር ቡድን በአገራችን ሽብር ለመፍጠር ሲሞክር በቁጥጥር ስር በመዋሉ ደስ ሊላቸው ሲገባ ፤አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር "የቡዱኑ መሪ ካልነገረኝ" አላምንም ብለው መናገራቸውና ከመንግስትና ህዝብ በላይ አሸባሪዎችና ሕገ ወጦችን እንደሚያምኑ በይፋ መናገራቸው...ወዘተ ሲታይ ተቃዋሚዎች ከባህሪያቸውና ድብቅ አጀንዳቸው ብሎም ከሕገ ወጥነታቸው የተነሳ ወንጀልነትን የማውገዝ ልምንድም ሆነ ባህሪይ እንደሌላቸው በግልፅ የሚያሳይ ነው፡ ፡ ይህ ደግሞ የመጣው አመራሮቹ ከድሮ አምነውበት የነበሩና ይዘውት ከመጡ የፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰባቸው ነው፡፡

በመግቢያዬ እንደገለፅኩት አንድ ሰው አከባቢውን ይመስላል፡፡ አከባቢው የፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የሰፈነበት ከሆነና ራሱ ግለሰቡም የዚሁ አስተሳሰብ አቀኝቃኝ ከነበረ ወደ ዴሞክራሲያዊ አየር የሰፈነበት ቦታ ሲመጣ ለመለማመድ ጊዜ እንደሚወስድ ቢታወቅም አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ግን ለመለወጥም ዝግጁ አለመሆናቸውና እስካሁን ባለው የአገራችን የዴሞክራሲ ሂደት ውስጥ ምንም ፋይዳ ሳይሰጡ ማለፋቸው ሊያስቆጫቸው ይገባል፡ ፡በቅርቡ አንድ ኤምባሲ ተቃዋሚዎችን ለማነጋገር ሲጋብዛቸው ብቻችን እንጂ ከእገሌ የሚባል ተቃዋሚ ፓርቲ ሆነን አንወያይም ማለታቸው ይታወቃል፡፡ከዛ

ፓርቲ ጋር አንወያይም ማለታቸው ምናልባት የዛው ፓርቲ መሪ በሃይለስላሴ ወይም በደርግ ጊዜ ስልጣን ስላልነበረው ይኾን?

እነዚህ ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዝግጁነት የሌላቸው አመራሮች ሕገ መንግስቱ በሰጣቸው መብት ተጠቅመው የተለያዩ ፓርቲዎች መስርተው ነገር ግን አመለካከታቸው አሁንም የድሮ ስርዓትን መናፈቅ ስለሆነ አበው ሲተርቱ ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም እንደሚሉት ሁሉ መቀየር ያለበት የፓርቲ ስም ሳይሆን አመለካከታቸው ነው፡፡ትክክለኛ ፖሊሲና ስትራተጂ ቀርፀው በመደማመጥና በመቻቻል ተክነው ለአገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ አጋር እንዲሆኑ እመኝላቸዋለሁ፡፡ሰላም!